# ስደተኛ ወያኔ ግንቦት 7




እድሜ ለብርሃኑ ነጋ እና አንዳርጋቸው  ታማኝ በየነ *በያን*  ኦነግን ትልቅ ያስመሰለው የግንቦት 7 እና የአሽቃባጮቹ ወሬ ነው:: ኦነግ ካሉት በታች ከሞቱት በላይ (ያውም በስም) ሆኖ የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው:: ይህ ድርጅት የኦሮሞን ሙብት ለማስጠበቅ የቆመ ሳይሆን ሻቢያንና ሌሎች የኢትዮጵያን ጠላቶች ለማስደሰት የሚሰራ_ ኦሮሞ በኢትዮጵያዊነቱ ኮርቶ የሚኖር ህዝብ መሆኑን ክዶ ከባዶ ነገር በመነሳት ኦሮሞን ታሪክ የሌለው በባርነት የሚኖርና የተዋረደ እንደሆነ አድርጎ የሚያቀርበው፣ ስለሆነ የኦነግ ጠላት እንጅ መሪ ሊሆን ከቶ አይችልም::ኦነግ እድል አያገኝም እንጅ እድል ቢያገኝ እጅግ የከፋ ጥፋት በሀገርና በህዝብ ላይ የሚያደርስ ቡድን ሊሆን እንደሚችል ካለፉት ተግባሮቹ በመነሳት መገመት ይቻላል:: ኦነግ ሸብር ለመፍጠር ሲባል ብቻና አገራችን የተረጋጋች እንዳትሆን ለማድረግ በተለላኪነት የሚሰራ እንጅ በራሱ ነፍስ ያለው ድርጅት አይደለም:: ተከታዮቹም ምንነቱን ያልተረዱና ኦነግ የሚያራምደው ፖለቲካ መቸም ቢሆን በተግባር ሊውል እንደማይችል ያልገባቸው ናቸው:: ኦነግ ኦሮሚያ የሚል የህልም አገር ፈጥሮ ያችን በህልሙ የፈጠራትን አለም እውን ለማድረግ የሚፍጨረጨር ድርጅት ነው:: ኦሮሚያ የምትባለዋ ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ በታሪክም ሆነ በካርታ የማትታወቅ ናት:: ማለትም ኦነግ በዜሮ መሰረት ላይ ድርጅቱን የገነባ: በህልም አለም ያለና አሁንም ያልነቃ በልዩነት ላይ አተኩሮ የሚሰራ እኩይ ድርጅት ነው ማለት ነው:: ይብላኝ እሹሩሩ ለሚሉት እኛስ እናውቀዋለን የትም አይደርስም:: የኢትዮጵያ ባንዲራም ሆነ የኢትዮጵያ ስም ኦነግን ለማስደሰት ሲባል ሊፋቅ የማይችል የህዝባችን የዘመናት የትግልና የመሰውእትነት ውጤት ናቸው:: ኦነግ በህይወት የሚኖረው ወያኔ በስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ብቻ ነው:: ወያኔ ሲጠፋ ኦነግም ይጠፋል ለዚህ ነው የተለያዩ መስለው በተግባር ግን የወያኔን መስመር ተከትሎ መቸም እውን ሊሆን የማይችል አላማ አንግቦ በአንድነት ሀይሎች ላይ የዘመተው:: ብዙወች ደጋፊወቹም በውጭ አገር ያሉና የፖለቲካ ጥገኝነት ለማግኘት ሲሉ ብቻ የሚያጭበረብሩት ናቸው:: ኦነግ ወይም ኦብነግ የወያኔ ተቀጽላወች እንጅ አጋር ሊሆኑ እንደማይችሉ ታምኖ ቢሰራ ይበጃል::  ብርሃኑ ነጋ እና አንዳርጋቸው  አንቀጽ 39  እንደሚጠቅም ለፓልቶክ ከረንት ሩም  ማሳመናቸው እጅግ ያስገርማል።

**ቶሎሳ ሳያ**